**7ኛው ሳምንት፡ የአብርሃም ጥሪ እና የተስፋው ቃል**

**የታሪክ**

**እጥፋት**፡-ዘፍጥረት 12 በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የለውጥ ምዕራፍ ነው። ከኃጢያት መስፋፋት፣ ከጥፋት ውሃ እና ከባቤል ግንብ አመጽ በኋላ፣ እግዚአብሔር የማዳን መንገድ መስመሩን መዘርጋት የጀመረበት

ነው። ስለሆነም እግዚአብሔር አሕዛብን ሁሉ ይባርክ ዘንድ **አንድ ሰው መረጠ**።ለዚህ

ነው አዲስ ኪዳን ወንጌልን ለማስረዳት በተደጋጋሚ ወደዚህ ክፍል የሚመልሰን። በዚህ ሽግግር እግዚአብሔር ለአብርሃም **የገባው ቃል ኪዳን** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ሒደቶች ሁሉ አንድ ቅርጽ እንዲሰጥ አድርጎአል።

ዘፍጥረት 12፡1-9

***ሥነ-መለኮታዊ ጭብጦች፡*** ምርጫና፣ ቃል ኪዳን

**ዋናው ሐሳብ፡** በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ አንድን ሰው እግዚአብሔር መረጠ እርሱም አብርሃም ይባላል፣ በእርሱም አሕዛብን ሁሉ ለመባረክ የማዳን እቅዱን እግዚአብሔር ይጀምራል።

## ዘፍጥረት 12:1— ጥሪ (ምርጫ)

እግዚአብሔር አብራም አገሩን፣ ቤተሰቡን እና የአባቱን ቤት ለቆ እርሱ ወደሚያሳየው ምድር እንዲሄድ ነግሮታል።ይህም ንጹህ **መለኮታዊ ተነሳሽነት** ነው።ምክንያቱም አብራም እግዚአብሔርን አልፈለገም ነገር ግን እግዚአብሔር አብራምን መረጠው እንጂ። በዚህ ምርጫ ውስጥ ለአብራም የተሰጠው ትዕዛዝ

መፈጸም **ጠንካር እምነትን** መኖርን ያካትታል ምክንያቱም አብራም እንዲሄድ ተጠየቀው፡-

**የእርሱ ሀገሩን(ደህንነት)** ፣**ቤተሰቡን (ማንነት)** ፣ትቶ መውጣትን የሚጠይቅ ስለነበር። ስለእርሱ የወደፊት ሁኔታ (እርግጠኝነት)አልነበርውም

ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለ መድረሻው በዝርዝር አልነገረውም **ቃል ኪዳን** ብቻ ገባለት እንጂ።

**ሥነ-መለኮታዊ አጽንዖት (ምርጫ)**፡-የእግዚአብሔር **ምርጫ ፀጋ** ነው እንጂ በሰው ጥረት ወይም መልካም ስራ የተገኘ አይደለም። ምርጫ ከመታዘዝ ይቀድማል አብራም ታዘዘ ምክንያቱም እግዚአብሔ ር ስለመረጠው። ይህ እውነት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚታየውን አብነት ያስቀምጣል ማለትም እግዚአብሔር አስቀድሞ ይጠራል ከዚያም በጊዜ ሂደት እቅዱን ይገልጣል የሚለውን ።

**ዘፍ12:1 ከአዲስ ኪዳን ጋር**

**ያለው ግንኙነት** ሮሜ 4፡ የአብርሃምን መጠራትና በኋላም የጸደቀው በስራ ሳይሆን በእምነት መሆኑን በማርጋገጥ የክፍሉን አዲስ ኪዳናዊ ትርጉም ወይም ብርሀን ይሰጠናል።ይህም የሚያርጋግጠው መዳን የሚጀምረው በሰው ጥረት ሳይሆን በእግዚአብሔር ተነሳሽነት ነው የ ሚለውን እውነት ነው።። የእግዚአብሔር **ጥሪ** ሁልጊዜ **ከመታዘዛችን** ይቀድማልና።

**ዘፍጥረት 12:2—እግዚአብሔር ለአብራም የተገባው ተስፋ**

እግዚአብሔር አብራምን ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርገው፣ እንደሚባርከው፣ ስሙንም ታላቅ እ ንደሚያደርግ ቃል ገብቷል። ቁልፍ ዝርዝሮችና ሶስት ዋና ተስፋዎች፡- አብራም ልጅ ባይኖረው ም **ታላቅ ሕዝብ** እንድሚሆን ተነገረው → የግል በረከት → የእግዚአብሔር ሞገስ፣ ጥበቃ እና አቅርቦት ከእርሱ ጋር እንደሚሆን ተነገረው። **ታላቅ ስም እንደሚኖርው** ተነገረው ይህም→ ከባቤል (ዘፍጥረት 11) ጋር ይቃረናል፣ እሱም ሰዎች ለራሳቸው ስም ለማስጠራት ሲ ሞከሩ ነበር።

**ሥነ-መለኮታዊ አጽንዖት** (**ተስፋ**)፡-

የእግዚአብሔር ተስፋዎች የሰውን የማይቻል ነገር ያሸንፋሉ። በረከት ለአብራም ጥቅም ብቻ ሳ ይሆን ነገር ግን ዓላማም አለው። እግዚአብሔር የሰውን ትዕቢት በመለኮታዊ ጸጋ ይቀየራል።

**ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ግንኙነት:-**

የእግዚአብሔር ዓላማ አሕዛብን ሁሉ መቤዠት ነው። ገላ 3፡8፡ ይህ

የቅዱሳት መጻሕፍት የንባብ ክፍል ለአብርሃም ወንጌል አስቀድሞ በእግዚአብሔር

እንደተሰበከልት ይነግርናል። ወንጌል በዘፍጥረት **በዘር መልክ** ተነግሯል።ለዚህ

ነው **የብሉይ ኪዳን ተስፋ የአዲስ ኪዳን ወንጌል የሆነው።**

**አብርሃም በተስፋ አመነ**።ሮሜ 4፡18-21፡ ምንም እንኳን በውቅቱ በነበሩት ሁኔታዎችና እግዚአብሔር ለአብርሀም በተናገርው ቃል መካከልትቃርኖ ቢኖርም አብርሀም በእግዚአብሔር **ቃል ኪዳን ሳይጠራጥር** እንዳመነ ይህ ክፍል ያርጋግጥልናል።ከዚህ

እንደምንመለከተው እምነት በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ መተማመን እንጂ በሚታዩ ማስረጃዎ ች ላይ መተማመን ማለት አይደለም።

**ዘፍጥረት 12:3 — የተስፋው ቃል ዓለም አቀፍ ወሰን**

እግዚአብሔር አብራምን የሚባርኩትን እንደሚባርክ፣ አብራምን ሚቃወሙት ወይም የሚርግሙት

ደግሞ እንደሚርግም፣እዲሁም በእርሱ አሕዛብን ሁሉ እንደሚባርክ ቃል ገብቷል። **ቁልፍ ዝር ዝሮች** አብራም ተወካይ ሆነ -አብራም እንድ እርሱ ለእግዚአብሔር በእምነት ምላሽ ለሚስጡ ሰዎች ውኪልን ምልክት ሆነ።በዚህ ተስፋ

ውስጥ የመጨረሻው ሐረግ ወሳኝ ነው: **"የምድር ሕዝቦች ሁሉ"** የሚልው።ምክንያቱም ይህ **የእግዚአብሔር ተልእኮ** ለአሕዛብ የመጀመሪያው ግልጽ መግለጫ ነውና።

***ሥነ-መለኮታዊ አጽንዖት (ቤዛነት)፡-***

የእግዚአብሔር እቅድ በአንድ ህዝብ ብቻ የተገደበ አይደለም። ይህ ቁጥር ስለ ወደፊት የሚያ መለከተው፡-በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ የእስራኤል ሚና ምን እንደሆነ፣ይህ ተስፋ በመጨረሻ የተፈጸመው የአብርሃም ዘር በሆነው በኢየሱስ ነው።ይህም የሚያስገነዝብን ምርጫ ተልእኮዊ እንጂ በአንድ ህዝብ ብቻ ይተገደበ አለመሆኑን ነው።

**በክርስቶስ ፍጻሜ ያገኘው የተስፋው ዓለም አቀፍ ወሰን (ሮሜ እና ገላትያ)**

**ሀ. በእምነት መጽደቅ**

ሮሜ 4፡3፡ አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጻድቅም ሆኖ ተቆጠረለት። መዳን ሁል ጊዜ በእ ምነት እንጂ ህግን በመጠበቅ የሚገኝ አይደለም።

**ለ.እውነተኛ የአብርሃም ልጅነት** በገላ 3፡7 እንደተገለጸው የአብርሃም አይነት እምነት ያላቸው የአብርሀም ልጆች ናቸው እንጂ በስጋ አይሁድ የሆኑት ሁሉ የአብርሀም ልጆች አይደሉም። የእግዚአብሔር ቤተሰብነት የሚገለጸው በመንፈሳዊ እውነት እንጂ በስጋ አይሁዳዊ በመሆን አይደለምና።

**ሐ. ክርስቶስ እንደ ተስፋው ቃል ዘር** ገላትያ 3፡16፡ለአብርሀም የተነገርው የተስፋው ቃል ዘር የሚያመለክተው ክርስቶስ ኢየሱስን ነው። አብርሃም ሊጠብቀው የሚችለው ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ፍጻሜ አግኝቷል። ኢየሱስ የዘፍጥረት 12 ፍጻሜ ነውና።

**ትልቁ የሥነ-መለኮትሥዕል**

**ምርጫ፡** እግዚአብሔር አብራምን የቃል ኪዳኑ እቅድ መነሻ አድርጎ መረጠው።

**የተስፋ ቃል፡-** እግዚአብሔር ከአብራም ጋር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ቃል ኪዳን አግርጎአል።

**ቤዛነት**፡ የእግዚአብሔር አላማ አለም አቀፋዊ ነው— በዘፍጥረት 3 ላይ የጠፋውን በረከት ወደ ነበረበት መመለስ።

**ጸጋ**፡- እግዚአብሔር ዓለምን መፈወስ ለመጀመር አንድ ፍጽምና የጎደለውን ሰው ይጠቀማል።

**ማጠቃለያ**፡-በዘፍ 12 እግዚአብሔር አብራምን መጥራቱ የሚያሳየው የድነት ታሪክ የሚጀምረው በእግዚአብሔር **ቸር ምርጫ እና በተስፋዎቹ በኩል መሆኑን ነው**።ለአብርሀም የተሰጠው የተስፋ ቃል ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን **ለሁሉም ህዝቦች በረከትን እንደሚያመጣ ነው**።ይህ የእግዚአብሔርን የማዳን እቅድ ያስተዋውቃል።በአዲስ ኪዳን ደግሞ የሮሜ መጸሐፍ ያ እቅድ እንዴት እንደሚሰራ ያብራራል። የገላትያ መጸሐፍ ደግሞ ያንን እቅድ የሚቀበለው ማን እንደሆነ ያርጋግጥል።በአጠቃላይ እግዚአብሔር በዘፍ 12:1-3 ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ፍጻሜውን ያገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ነውና።